በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
የገቢዎች ባለሥልጣን
AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
REVENUE AUTHORITY
☎ 058-220-4694 or 058-220-4693
Fax 058-226-61 87/49 53
✉ 746

ቁጥር ገቢዎች ም.ዳ- 4-1611
Ref.No
ቀን 15/04/2007 ዓ.ም
Date

ለ 104 ዞን አስ/ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት
__________

ለ 37 ከተማ አስተ/ገቢዎች ጽ/ቤት
__________

ጉዳዩ:- <u>የሂሳብ መዝገብ ውድቅ ተደርጐ በቀን ገቢ ግምት ወይም በ3ኛ ወገን የግብይት መረጃ የሚወሰንባቸው የዱቄት ፋብሪካዎች ግብርና ታክስ አወሳሰን በሚመለከተ ማብራሪያ ለስለመስጠት፤</u>

ከላይ በርዕሱ እንተደገለፀው በክልላችን የሚገኙ የዱቄት ፋብሪካዎች በአገር አቀፍ ደረጃ በአለው የግብዓት እጥረት ምክንያት መንግስት ለህበረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ዱቄት እና ዳቦ ለማቅረብ በሚያስችል መንገድ በየደረጃው በሚገኙ ንግድ ቢሮ፣ መምሪያዎችና ጽ/ቤቶች በአካል ለፋብሪካዎች የስንዴ መግዣ እና የዱቄት መሸጫ ዋጋቸውን በመወሰን ለተጠቃሚው እንዲያቀርቡ ጥብቅ ክትትል፣ ቁጥጥር እና ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡

በዚህ መሠረት አብዛኞቹ የዱቄት ፋብሪካዎች ገቢ እና ወጪቸውን በተሟላ መንገድ የሂሳብ መዝገብ በመያዝ የግብርና ታክስ ግዴታቸውን እየተወጡ ይገኛሉ፡፡ አንዳንድ የዱቄት ፋብሪካዎች ደግሞ የተስተካከለ የሂሳብ መዝገብ ማቅረብ ባለመቻላቸው ምክንያት የአቀረቡት የሂሳብ መዝገብ ውድቅ እየተደረገ በቀን ገቢ ግምት ወይም በ3ኛ ወገን የግብይት መረጃ መሠረት የሚወሰነው የግብር ውሳኔ መንግስት የስንዴ መግዣ እና የዱቄት መሸጫ ዋጋ በወሰነው የትርፍ ህዳግ መሠረት እየገዛን እና እየሸጥን ከምናገኘው ትርፍ በላይ በሆነ የትርፍ ህዳግ እየተሰላ አለአግባብ ግብር እና ታክስ እንድንከፍል ተጠይቀናል የሚሉ ቅሬታዎች ከተለያዩ አካባቢዎች ለገቢ ተቋሙ ቀርቧል፡፡

ስለዚህ አምራች ዘርፉን ለማበረታታትና ፍትሃዊ ግብር እና ታክስ በትርፍ ህዳግ ላይ በመመስረት ለመወሰንና ለመሰብሰብ እንዲቻል የአሠራር አቅጣጫ ማስተላለፍ አስፈልጓል፡፡ ባለሀብቶች /የፋብሪካ ባሌቶች/ያቀረቡት የሂሳብ መዝገብ ተማዓኒነት ሳያጣበት ወይም የድርጅቱን እንቅስቃሴ የማይገልጽ ሆኖ ሲያገኝ የሂሳብ መዝገቡን ውድቅ አድርጐ በሦስተኛ ወገን ግብይት መረጃ ወይም በቀን ገቢ ግምት ጥናት መረጃ መሠረት ግብሩን የገቢ ተቋሙ መወሰን እንደሚችል በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 70 መሠረት የግብር ግዴታ እንዲወጡ ማድረግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ግብሩ መወሰን ያለበት መንግስት ስንዴ ምርት ዋጋ ወስኖ ለፋብሪካዎች የሚያቀረብ እና የስንዴ ምርት ዱቄት ዋጋ በብር ወስኖ ለህበረተሰቡ ለዳቦ ቤቶች እና ለሸማቾች ማህበራት እንዲከፋፈል እያደረገ ከሆነ ግብር ከፋዩ ባላገኘው ጥቅም ላይ ግብር መክፈል ስለሌለበት የትርፍ ህዳግ በመንግስት የዋጋ ውሳኔ የተሸጠ ወይም እንዲከፋፈል የተደረገ የዱቄት ምርት ዋጋ በብር ሲቀነስ በመንግስት አቅርቦት ለፋብሪካዎች የተሠጠ የስንዴ ምርት ዋጋ በብር ሆኖ ባለፋብሪካዎች ባገኙት ገቢ ላይ ተመስርቶ መወሰንና መሰብሰብ አለበት፡፡